በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ - ክፍል 1

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ
**E-mail:** kesisolomon3@gmail.com

*ቦታ፦* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

**መጋቢት ፳፱ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም.**

# ጋብቻ

- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ “የጋብቻ ምስጢር ባልና ሚስትን ከምድራዊነት አውጥቶ እግዚአብሔርን ወደ መምሰል የሚያደርሳቸውታላቅ ምስጢር ነው።” ብሎ አስተምሮናል፡፡

- ቅዱስ ጳውሎስም በመልዕክቶቹ “ይህ ምስጢር ታላቅ ነው፣ ጋብቻ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ነው” በማለት ስለ ጋብቻ ምስጢር ገልጦልናል፡፡

- በእግዚአብሔር ፈቃድ ይህን ትምህርት በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስናቀርብ ከፍተኛ ደስታ እየተሰማን ሲሆን ይህ ትምህርት ለእጮናሞች፣ አዲስ ለተጋቡ ሙሽሮች፣ ወይም ትዳራቸው ጤናማ እንዲሆን ለሚሹ ሁሉ የተዘጋጀ መሆኑን ከመግለጽ ጋር ነው፡፡

- ይህ ትምህርት አሥራ አምስት ክፍሎች የሚኖሩት ሲሆን በተቻለ መጠን በማዋሐድ አሳጥረን ለማቅረብ እንሞክራለን፡፡ ትምህርቱ በይዘቱ ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ጋብቻ የምታስተምረውን አስተምህሮ ለወደፊቱም ለመጠቀም እንዲያስችል ሆኖ የማስታወሻ ነጥቦችን ጋር ያካተተ ነው፡፡

- በእግዚአብሔር ፈቃድ ይህ ትምህርት ከ20 ዓመታት በላይ ለሆነ ጊዜ የተጠቀምንበት፣ በርካታ ኦርቶዶክሳውያን የታነጹበት፣ ትዳራቸውን የጠበቁበት ሲሆን አሁንም የሚማሩትና የሚጠቀሙበት ሁሉ በትዳራቸው የእግዚአብሔርን ክብር የሚገልጡበትና የትዳራቸውንም መልካም ውበት የሚጠብቁበት ያድርግልን፡፡

# ጋብቻ

## መግቢያ

- የዛሬውን ትምህርት ለጋብቻ የሚደረግን ዝግጅት አስመልክቶ ወይም ጋብቻቸውን በመልካም መሠረት ላይ ለማቆም ለሚሹና በጋብቻ ዙሪያ የተለያዩ ጥያቄዎች ላላቸውና ምላሽ ሊሆናቸው በሚችለው ክፍል እንጀምራለን፡፡

## በጋብቻ ዙራያ በዘመናችን ችግር አለ?

- አዎ አለ፡፡ ዘራ ከአንድ ወር ባነሰ ጊዜ ውስጥ ጋብቻቸውን የሚያፈርሱ አሉ፡፡
- ከዛሬ 10 ዓመት በፊት እስከ ስድስት ወር እንኳ የመቆየት እድሎች ነበሩ፡፡
- ከዛሬ ሃምሳ ዓመት በፊት ደግሞ ፍቺ በቤተ ክርስቲያን ብዙ አይሰማም ነበር፡፡ ቢኖርም እንኳ እንደ ሚያሳፍር ነገር ተቆጥሮ ሳይሰማ በምስጢር በድብቅ ሲደረግ የሚገጥም ነበር፡፡
- በዚህ ዘመን ጋብቻቸውን ለሚፈጽሙና ለፈጸሙት ሁሉ መጸለይ አለብን፡፡

## የቅድመ ጋብቻ ትምህርት ወይም ምክር አስፈላጊነት

- ይህ ጉዳይ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች የቅድመ ጋብቻ ትምህርትንና ምክርን በስፋት የመስጠት አስፈላጊነት የሚጠቁም ነው፡፡
- አንዳንዶች ይህን ትምህርት ካገቡ በኋላ ወይም አጋጣሚ ሲያገኙ ብቻ የሚከታተሉ ናቸው፡፡
- ይህን የጫጉላ ሽርሽርን እንዴት ማሳለፍ እንዳለባቸው በመጠየቅ የሚሸፍኑት አሉ፡፡ ስለጋብቻ መጠየቅ ችግር የለውም፡፡ ነገር ግን ከአንድ ወር ባነሰ ጊዜ ውስጥ ፍቺ ለመፈጸም መነሳት ስህተት ነው፡፡ በማንነታችን አለመጣጣም፣ ትዕግስት ማጣት፣ ነገርን በዝርዝር አርዝሞ የመግለጽ አሰልቺነት ቢኖርም ሁሉ በጤናማ መልክ የሚስተካከልበት መንገድ ግን የሚገኘው ከትምህርትና ምክር ነው፡፡

# ጋብቻ

<u>ምክሩን ማን ይስጠን?</u>

- የጋብቻ አማካሪነት ከኑዛዜና መንፈሳዊ ኅዳናን ከመጠቆም ይለያል፡፡
- ኃጢአታችንን የምንናዘዘው (Confession) ለንስሐ አባታችን ብቻ ነው፡፡ የንስሐ አባታችንም ሰምቶ መንፈሳዊ መፍትሔ ይሰጠናል፡፡
- የሕይወትን ኅዳና ማመልከት (Spiritual Guidance) ምስጢር አይደለም፡፡ በምዕመናንም በካህናትም ተሰጥኦው ባላቸው ሁሉ ሊፈጸም ይችላል፡፡
- ኦርቶዶክሳዊ የጋብቻ ሕይወት አማካሪነት (Marriage Counseling) ግን የሥነ መለኮት ትምህርት፣ ከአማካሪነት ትምህርት …ጋር አጣጥሞ በከፍተኛ ደረጃ መማርና በዕውቀት የዳበረ ችሎታን ይፈልጋል፡፡
- ክርስቲያናዊ የጋብቻ ሕይወት አማካሪነት በመደዴው ዓለም ከሚሰጠው አማካሪነት ይለያል፡፡
- በክርስቲያናዊ (ኦርቶዶክሳዊ) አማካሪነት እግዚአብሔር፣ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ መንፈሳዊ እሴቶች የምክሩ ማዕከል ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን የእግዚአብሔር በጋብቻው መኖር የማይቀሩ መሠረታዊ ሂደቶች ናቸው፡፡
- ስለዚህ ምክሩ ሲቀርብ ለምን እንደሚሰጠን፣ ምክሩ የሚሰጥበት ግብና፣ ከግቡም ለመድረስ የሚያስፈልጉ ዝግጅቶች ሁሉ መታወቅ መካተትና መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡
- ምክሩም በየመናፈሻው ሳይሆን ራሱን በቻለ ሥርዓት ባለው መንገድ አብነት ሊሆን ከሚችለው ሀገረ ስብከት አንስቶ በመላ ቤተ ክርስቲያኒቱ በሚገኙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የተስተካከለና የተሟላ ሥፍራ ከማዘጋጀት አንስቶ በተገቢው መንገድ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ይህ ከሆነ ጋብቻን በጊዜው መታደግ ያስችላል፡፡

# ጋብቻ

## የቅዱስ ጋብቻ (የፍቅር) ምስጢርነት

- ክርስቲያኖች ዘወትር ጌታችንን የምንመለከት፣ የምንሰማውና ከእርሱም የምንማር መሆን ይጠበቅብናል፡፡ በክርስቲያናዊ ጋብቻ እንዴት ማፍቀርና መኖር እንዳለብን ማወቅ የተጋቢዎች ሁሉ ግዴታ ነው፡፡
- ወደ ጌታችን እንመልከት፣ እንዴት መኖር እንዳለብንም ከእርሱ እንስማ፣ ጠባያችንም ምን መሆን እንዳለበት ከእርሱ እንማር፡፡ "ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፡፡" ብሎናልና የሕይወታችን ማዕከሉ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ <u>*ማቴ 11፡29፡፡*</u>
- ከሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ምስጢራት ታላቁ ምስጢር ተብሎ የተጠቀሰው የጋብቻ ምስጢር ነው፡፡
- "ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና፥ ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን፥ ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት፥ ይመግበዋል ይከባከበውማል። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፥ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ።" ኤፌ 5፡30-32፡፡
- ይህ ምስጢር ፈጽመን የማንተነትነው የማንመረምረው ታላቅ ምስጢር ነው፡፡ ተጋቢ እጮናሞቹ ከመጋባታቸው በፊት የክርስቶስ አካል ብልቶች ናቸው፡፡ ከተጋቡ በኋላ ደግሞ አንድ አካል ሆነው የክርስቶስ አካል ብልቶች ሆነው ይቀጥላሉ፡፡ ወንዱ ክርስቶስን ሰትዋ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን ይመስላሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያንም የክርስቶስ አካል ናት፡፡
- እግዚአብሔር አባትና እናትን ትተን በምስጢረ ጋብቻ እንዴት አንድ ስለመሆን አስተምሮናል፡፡

# ጋብቻ

**<u>የቅዱስ ጋብቻ (የፍቅር) ምስጢርነት…</u>**

- ይህም ዘፍጥ 2፡24፣ ማቴ 19፡5-6፣ ማር 10፡6-7፣ ኤፌ 5፡30-32 ተጠቅሷል፡፡

- የባልና ሚስትን አንድነት ለመረዳት የቤተ ክርስቲያንንና የክርስቶስን አንድነት መረዳት ያስፈልጋል፡፡

- ባልና ሚስቶች በግኑኝነታችን፣ በመቀራረባችን ዘወትር በየደቂቃው በየሰዓቱ እግዚአብሔር የአንድነትን ሥራ የሚሠራበት ምስጢር የጋብቻ ምስጢር ነው፡፡

- ይህ ምስጢር ለጊዜው በቦታ በመለያየት የተነሳ መንፈስ ቅዱስ የሚሰራው ሥራ የማይከፈልበት ያለ ማቋረጥ የሚቀጥል ምስጢር ነው፡፡

- ታዲያ ይህ ምስጢር ዝግጅት ያስፈልገዋል፡፡

- ለቅዱስ ቁርባን የምንዘጋጀው እንዴት ነው? ንስሐ በመግባት፡፡

# ጋብቻ

## *የጋብቻ ዝግጅት ቅደም ተከተሎች*

- የምናደርገው ዝግጅት ምንድር ነው? ተክሊል የምናደርግበትን ቤ/ክ መምረጥ፣ ድግሱ፣ አዳራሹ፣ የጫጉላ ሽርሽር ቦታው፣ መኖሪያ ቤታችን ዌወም ሠፈራችን፣… ነው? ሰዎች በጋብቻ ዝግጅት ብዙውን ጊዜ የምናጠፋው በዚህ ነው።
- ብንተጫጭም በታወረ የፍቅር ስሜት መነዳት ብዙዎቻችን ጋር ይኖራል። ዝግጅት ብለን የምናስበው ከላይ ከተቀሱት ጥቂቶች ተጫማሪ ቢኖር ፍቅር፣ ፍቅር፣ ፍቅር… የስሜት ፍቅር ነው። የትዳሩ ዕድሜ ማጠር፣ ትዳርን በንትርኩ ወይም መጥፎ በሆነው ገጽታ የመስበኩ ሕይወት ምንጩ የዝግጅት ማነስ ነው።
- በርካታዎች ከጋብቻ ወይም ከሠርግ በፊትና በኋላ ያለው ሕይወት የተለያየ እንደሆነ ከቀደሙት አይማሩም። ገብተውበት ከወር ባነሰ ጊዜ ወደ ንስሐ አባቶቻቸው በመሄድ ያገባሁት/ያገባኹት እርሱ/ሷ አይደለም/ለችም፤ ይመልከቱ ከበፊቱ የተለየ/የች ነው/ናት ብለው እስኪጮሁ ድረስ አምነው አይዘጋጁም።
- ሰባት ሰዓት አብራችሁ ቁጭ ብላችሁ በመታገስ የምታወሩ ባለትዳሮች አላችሁ? የማትችሉም አላችሁ። ነገር ግን ለምን? ከማግባት በፊት እንዲህ ነበርን? ጠባያችንስ እንደልቡ እንዲለዋወጥ ስሜትስ እንዲገዛንና እንዲመራን ስለምን ሆንን?

# ጋብቻ

## *የጋብቻ ዝግጅት ቅደም ተከተሎች…*

- ተጋቢዎች በትዳር ሕይወታችን፣ በገንዘባችን፣ በትምህርት፣ በማኅበራዊ ሕይወታችን፣ በልጆቻችንና በአስተዳደጋቸው ፣ አብሮን እንዲኖር በምንፈቅድለት ዘመድ ወይም ወዳጅ፣ ፈቃዳችንን በምንፈጽምበት ሁኔታ ሁሉና ወዘተ … ሥርዓትና አቅጣጫ ሊኖረን ይገባል፡፡
- ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያናዊ ጋብቻን፣ መተጫጨትን፣ ትዳርን ፣ ፍቺን፣ የልጆች አስተዳደግን አስመልክቶ በቤተ ክርስቲያናችን የሚገኘውን ትምህርት በአግባብ መረዳት አለብን፡፡
- በትዳር ሕይወት ቤቱ የሚመራው በማነው? **የእያንዳንዱስ ድርሻ ምንድር ነው?… ይህን አስመልክቶ የተለያዩ ክርክሮች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ግን እግዚአብሔር የሚለውን እንነግራችኋለን፡፡**
- **ለጋብቻ ሕይወት ትልቁ ትምህርት ቤት ኦርቶዶክሳዊ ወላጅ ራሱ ነው፡፡ አዲስ ተጋቢዎች ወላጆቹ ምን ያህል በሕይወታቸው ክርስቶስን እንደሚመስሉ በመመርመር ልጁ/ልጅቱ ለትዳር ያላቸውን ብቃት መገምገም ይችላሉ፡፡ የሚመረመረው የወላጆቻቸው ሀብት ቁሳቁስ አይደለም ሕይወታቸው እንጂ፡፡ ወላጆችስ የኛ በትዳር ተስተካክሎ አለመኖር የልጆቻችን የጋብቻ ሕይወት መሰናክል ሊሆን እንደሚችል እናውቃለን?**
- **መልካም ወላጆችን መርምሮ ለማወቅ የንስሐ አባቶችን ጠይቁ፡፡ ልጆቻቸውን ስለሚያውቁ ይነግሯችኋል፡፡**

# ጋብቻ

***የጋብቻ ዝግጅት ቅደም ተከተሎች…***

**ከመተጫቸት በፊት**

- ሴቲቱ ነቅዕ እንደ ሌለበት ጎብስት ወንዱ ብልሽት እንዳልነካው ወይን ሆነው በቤተ ክርስቲያን የአምላካቸውን ፈቃድ እያወቁና እያደረጉ በንጽሕና መቆየት ይኖርባቸዋል፡፡
- ልጅ ከመወለዱ በፊት አሳብ እንደሚወለድ ሁሉ ሐሳቡ ከንጽሕና ጋር ራሱን ለቤተ ክርስቲያን የሰጠ ክርስቶስን እየመሰሉ ይቆያሉ፡፡

**መተጫጨት**

- መንፈሳዊ፣ ልቦናዊ፣ አካላዊ፣ ስሜታዊ ብስለትን በመመርመር መወሰን፡፡

**ቅዱስ ጋብቻ (ምስጢረ ተክሊል)**

- ጋብቻ ተጋቢዎቹ የሚንከባከቡት ከመተጫጨት በፊት አስበው፣ በመተጫጨት ጸንሰው ምስጢረ ተክሊል በተፈጸመበት ዕለት የሚወልዱት የመጀመሪያ ልጅ ነው፡፡
- በሥጋ የሚወለድ ልጅ እንክብካቤ እንደሚያስፈልገው ይህ ምስጢረ ተክሊል በተፈጸመበት ዕለት የተወለደው ልጅ - ጋብቻ እንክብካቤ ያስፈልገዋል፡፡
- በሥጋ የሚወለድ ልጅ በሽታ እንደሚያጋጥመው ይህ ምስጢረ ተክሊል በተፈጸመበት ዕለት የተወለደው ልጅ - ጋብቻ የተጋቢዎቹን ግኑኙነት የሚያበላሹ በሽታዎች ይገትሙታልና መተከምና መዳን ያስፈልገዋል፡፡ ሲታመምም ሊያክሙት የሚችሉ በርካታ ሐኪሞች አሉ፡- የንስሐ አባት፣ ኦርቶዶክሳውያን መካሪዎች… የትዳር ጤንነቱ ይመለስ ዘንድ እግዚአብሔር ያስችላቸዋል፡፡

# ጋብቻ

*<u>የጋብቻ ዝግጅት ቅደም ተከተሎች... ቅዱስ ጋብቻ (ምስጢረ ተክሊል)...</u>*

- ልጅ እጁ አንገቱ ቢታመም እጁ አንገቱ ይቆረጥ እንደማንለው ሁሉ ጋብቻም መመቆረት ይፍረስ ማለት አይገባም ማሳከም እንጂ፡፡
- ጋብቻ በጤንነት ለመኖር ርኅራኄን፣ ወዳጅነትን፣ የጋብቻውን ፍላጎት መሟላት ይሻል፡፡
- በክርስቶስ አንድ የሆኑትን ሊለይ የሚፈልገው ሰይጣን ነው፡፡ ሰይጣን ትዳሩን ለማፍረስ የተቻለውን ብልጠት ሁሉ ይጠቀማል፡፡ ስለዚህ ዘወትር ጌታችንን የምንመለከት፣ የምንሰማውና ከርሱም የምንማር እንሁን፡፡ ይህም ትምህርት ካማግባት አስቀድሞም ሆነ ካገቡ በኋላ ስለጋብቻ ጠንቅቆ አውቆ የጋብቻን ሕሐሐወት መንከባከብ ነው፡፡
- ብዙዎች ይህን ትምህርት ላለመማር በአእምሮአቸው ባደረ ሰይጣን አደፋፋሪነት ዌወም በኩራት ምክንያት ያበዛሉ ትምህርቶችንና ምክሮችንም ይንቃሉ፡፡ እንዲህም እየኖሩ በቤተ ክርስቲተተን አግብተው በፍርድ ቤት ተፋተው ከፈቱ ከወራት ዌወም ዓመታት በኋላ ከተደበቁበት ወጥተው መፍታታቸውን ለንስሐ አባታቸው በመንገር ለታላቁ ምስጢር ለጋብቻ እንቅፋት ያኖራሉ፡፡
- በ1ኛ ቆሮ 11፡18-34 ለቅዱስ ቁርባን የሚያስፈልገውን ቅድመ ዝግጅት ይነግረንና ለጋብቻም የሚያስፈልገውን ዝግጅት እንድናውቅ ያሳስበናል፡፡ “ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልምና። ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ አያሌዎችም አንቀላፍተዋል። ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም ነበር፤ ነገር ግን በተፈረደብን ጊዜ ከዓለም ጋር እንዳንኮነን በጌታ እንገሠጻለን።”
- ሳሰሰገባቸው የሚቆርቡት የምስጢሩ ምንነት ያልገባቸው፣ አምልኮተ ቤተ ክርስቲያንን የማይፈጽሙ ዝግጅትና መርሐ ግብር የሌላቸው ናቸው፡፡ ታዲያ እነዚህ ፍርድን ይቀበላሉ፡፡ በራሳቸው ቢፈርዱ ንስሐ ገብተው ቀኖናቸው (ቅጣታቸውን) ቢፈጽሙና ቢስተካከሉ ከፍርድ ያመልጡ ነበር፡፡
- በጋብቻም ጌታቸውን በቤታቸው የማይቀበሉ፣ በመካከላቸውም ይሆን ዘንድ የማይፈቅዱ የማመመውቁትም አሉ፡፡

# ጋብቻ

*__የጋብቻ ሦስቱ ገጽታዎች__*

- *ጋብቻ የተመሠረተው በኤደን ገነት ሲሆን በሐዲስ ኪዳንም በቃና ዘገሊላ መልሶ እንደባረከውና እንዳደሰው ከበደል በፊት ወደነበረበት ሁኔታ እንደመለሰው ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲሁም የቤተ ክርስቲያናችን አባቶች ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅና ቅዱስ አውግስጢኖስ ገልጠዋል። __ዘፍጥ 2፡18-25፣ ዮሐ 2፡1-11።__*
- በቃና ዘገሊላ ውሃው ወደዌወን ከመለወጡ በፊት የነበረው ስሜታዊ ፍቅርን ሲመስል ከተለወጠ በኋላ ያለው ደግሞ በመሥዋዕትነት ላለለ የተመሠረተውን ፍቅር ይመስላል።
- ክርስቲያናዊ ጋብቻ በመሥዋዕትነት ላለለ የተመሠረተ ነው። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ የተባለውም ለዚሁ ነው። *__ኤፌ 5፡25።__*
- የጋብቻ ሦስቱ ገጽታዎች መተው፣ አንድ መሆንና መረዳዳት ናቸው። *__ዘፍጥ 2፡24-25፣ ማቴ 19፡3-12፣ ማር 10፡2-12፣ ኤፌ 5፡31__*
- ልጆቻችን በጋብቻ ሕይወት አባትና እናታቸውን እንዲተው የምንፈቅደው መቼ ነው? ከ18 ዓመት ጀምሮ ነው።
- ድንገት በሚያገቡበት ቀን ውጡ አንበላቸው። በስሜት እንዲበስሉ በቂ ዝግጅትም እንዲኖራቸው እናድርጋቸው።
- ትተውናል ማለት አያከብሩንም ማለት ኤአደለም። ግን መውጣት ያስፈልጋቸዋል። ካልተው ወደፊት አንድ ወደ ሚያደርገው ጋብቻ ከዚያም ወደ መረዳዳት ሊደርሱ አይችሉም።
- ከ18 ዓመት ዕድሜያቸው በፊት ስሜታዊ፣ መንፈሳዊ፣ ፍትወታዊ፣ የመግባባት፣ ወዘተ ምሳሌነታችንን እናሳያቸው። ከ18 እስከ 25/30 ዓመታቸው ድረስ በደንብ እንዲጸኑ እናድርጋቸው። እነርሱም በኋላ ተንከባከቡ ሲባሉ ኤአከብዳቸውምና። ዝግጅቱ ካለ ይደሰታሉ።
- ሰው አባትና እናቱን በመተው ከሚስቱ ጋር አንድ የሚሆነው በፍቅር ነው።
- የመጀመሪያው አፍቃሪ ጌታችን መድኃኔዓለም እንደሆነ ሁሉ በጋብቻም ለፍቅር መቅደም ያለበት ባል ነው። ሚስትም ከባልዋ የተቀበለችውን መልሳ ለባልዋ ትሰጠዋለች። *__1ኛ ቆሮ 7፡3።__*

# ጋብቻ

*የጋብቻ ሦስቱ ገጽታዎች*

*1. መተው*

- አንድ ከመሆናችን በፊት መተው ተገቢ ነው፡፡
- ቅድሚያውን ለትዳር አጋራችን መስጠት ይኖርብናል፡፡
- የምንተወውን ማወቅ አለብን፡፡
- እንቅፋቶቹን አውቆ ማለፍና መተው
- ያለመተው ከሚያስከትላቸው ችግሮች አንዱ የቤተሰቦች በትዳር ጣልቃ መግባትና ትዳሩን መበደል ነው፡፡
- ለመተው ከሚረዱን ዘዴዎች መካከል አንዱ ከልጅነት ጀምሮ ዝግጅት ማድረግ ነው፡፡

*2. አንድ መሆን*

- አንድነቱ ጸንቶ የሚኖረው ባሎችም ሚስቶችም ድርሻቸውን ማወቅ፡፡ ኤፌ 5፡22-33፡፡
- አንድነቱ ጸንቶ የሚኖረው የሚከተሉትን አምስቱን ቃልኪዳኖች ዘወትር መጠበቅ
  - እግዚአብሔር አንድ ደደደረገውን ላለመለየት ቃል በመግባት፡፡ መቴ 19፡6
  - በመውደድና በማክበር
  - ደግና ርኅሩኅ የትዳር አጋር በመኖን
  - ዘወትር በመስጠት፣ ይቅር በማለት የጋብቻን ፍላጎት በማሟላት
  - የተቀደሰውን እግዚአብሔር የሚወደውን ሕይወት ለመያዝ ዘወትር ደካማነታችንን ወይም ደካማ ጎናችንን በመለወጥ ወይም በማሻሻል ነው፡፡

# ጋብቻ

*የጋብቻ ሦስቱ ገጽታዎች*

*1. መተው*

- አንድ ከመሆናችን በፊት መተው ተገቢ ነው፡፡
- ቅድሚያውን ለትዳር አጋራችን መስጠት ይኖርብናል፡፡
- የምንተወውን ማወቅ አለብን፡፡
- እንቅፋቶቹን አውቆ ማለፍና መተው
- ያለመተው ከሚያስከትላቸው ችግሮች አንዱ የቤተሰቦች በትዳር ጣልቃ መግባትና ትዳሩን መበደል ነው፡፡
- ለመተው ከሚረዱን ዘዴዎች መካከል አንዱ ከልጅነት ጀምሮ ዝግጅት ማድረግ ነው፡፡

*2. አንድ መሆን*

- አንድነቱ ጸንቶ የሚኖረው ባሎችም ሚስቶችም ድርሻቸውን ማወቅ፡፡ ኤፌ 5፡22-33፡፡
- አንድነቱ ጸንቶ የሚኖረው የሚከተሉትን አምስቱን ቃልኪዳኖች ዘወትር መጠበቅ
    - እግዚአብሔር አንድ ደደደረገውን ላለመለየት ቃል በመግባት፡፡ መቴ 19፡6
    - በመውደድና በማክበር
    - ደግና ርኅሩኅ ከራስ ይልቅ የሌላውን ጥቅም የሚያስቀድም/የምታ የትዳር አጋር በመሆን
    - ዘወትር በመስጠት፣ ይቅር በማለት የጋብቻን ፍላጎት በማሟላት
    - የተቀደሰውን እግዚአብሔር የሚወደውን ሕይወት ለመያዝ ዘወትር ደካማነታችንን ወይም ደካማ ጎናችንን በመለወጥ ወይም በማሻሻል ነው፡፡

# ጋብቻ

*የጋብቻ ሦስቱ ገጽታዎች*

*3. መረዳዳት*

- አንድነቱ የበለጠ ጥልቅ ስለሚሆን በሰማይ ወንድ ሴት የሚል ጾታ እንደሌለ ሁሉ በእርሱ በእግዚአብሔር በምድር የሚገኙ የእግዚአብሔር ይሆናሉ፡፡

- ደካማውን ሥጋ ለማሸነፍ በሁሉ መረዳዳት፡፡

- ቀጣይነትና ተከታታይነት ባለው መንገድ ሁለቱ አንድ ሆነው ተሳስረው መረዳዳት ናቸው፡፡

የዚህ ትምህርት ዓላማዎች

- የቅድመ ጋብቻን ትምህርትና ምክር አስፈላጊነት ማስገንዘብ
- የጋብቻን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት መረዳት
- ተጋቢዎች በዘወትር ህይወታቸው የሚገጥሟቸውን ችግሮችና ፈተናዎች ማስረዳት
- ለመተጫጨት፣ ለጋብቻ፣ ለፍቺ ወዘተ ቤተ ክርስቲያን የምትሰጣቸውን ትምህርቶች መረዳት ነው፡፡

... ክፍል ሁለት ይቀጥላል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።